# <u>በሜትሮሎጂ ጽንሰ ሃሳብ ላይ በቋሚ የሬዲዮ ፕሮግራም የተላለፈ ጽሑፍ</u>

*<u>የሥርጭት ቀን</u>: ግንቦት 19/1991ዓ.ም.*

## *ሜትሮሎጂ ምን ማለት ነው?*

የአለካክ ጥበብ ራሱን የቻለ አንድ የሳይንስ ዘርፍ ሆኖ ሜትሮሎጂ በመባል ይታወቃል። ሜትሮሎጂ "ሜትር" እና "ሎጂ" ከተባሉ ሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን፣ "ሜትር" ማለት መለኪያ፣ "ሎጂ" ደግሞ ዕውቀት ማለት ነው። ሁለቱ ቃላት ተጣምረው "ሜትሮሎጂ" ማለትም "የአለካክ ሳይንስ" የሚለውን ትርጉም ይሰጡናል።

"ሜትሮሎጂ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ሲነገር ከምንሰማው ከ"ሚ ቲ ዎ ሮ ሎ ጂ" የተለየ ትርጉም እንዳለው አድማጮች በውል ሊገነዘቡት ይገባል።

ብዙውን ጊዜ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ከዜና ቀጥሎ የምንሰማው "ሚ ቲ ዎ ሮ ሎ ጂ" የአየር ንብረትንና የአየር ጠባይን ጨምሮ በውስጡ ያሉ ክስተቶችን የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን፣ የአለካክ ሳይንስ ከሆነው ከ"ሜትሮሎጂ" በእጅጉ የተለየ ጽንሰ–ሐሳብ እንደሆነ በቅድሚያ መረዳት ይኖርብናል። ስለሆነም "ሚ ቲ ዎ ሮ ሎ ጂ" የቀኑን ከፍተኛና ዝቅተኛ ሙቀት፣ ፀሐያማ ወይም ዝናባማነት በመተንበይ መረጃዎች የሚሰጠን ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ስለሜትሮሎጂ ስናወሳ ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ትስስትር ያለውን የአለካክ ሳይንስ ማለታችን ነው።

ዕውቀት እየሰፋ፣ ሥልጣኔ እየገፋ በሄደበት በዚህ ዘመን በዓለም ዙሪያ ያሉ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩና የተለያዩ ባሕሎች ያሏቸው ሕዝቦች በሚያደርጉት የንግድም ሆነ የቴክኖሎጂ ልውውጥ መግባባት የቻሉት የአለካክ ሳይንስ ወይም ሜትሮሎጂ ባስገኘላቸው ዓለም አቀፍ ቋንቋ አማካኝነት ነው። ዛሬ በዓለማችን የአገሮች የዕድገት ደረጃም የሚመዘነው በሜትሮሎጂ ዘርፍ ከሚያሳዩት ዕድገት አንፃር እየሆነ መጥቷል። መለካት ማወቅ፣ ማወቅም መሻሻል ነውና።

ለዘመናት የተደረጉ የጋራ ጥረቶች የመሥፈሪያና የመለኪያ መሣሪያዎች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ተመሳሳይ የአለካክ ሥርዓት እንዲፈጠር በማስቻላቸው መሠረታዊ–አሀዶች ሰባት እንዲሆኑና ለእያንዳንዳቸው አንድ ዓይነት የአለካክ ዘዴ ብቻ እንዲኖር እንዲሁም ኃይልን፣ ግፊትንና የመሳሰሉትን ለመለካት ደግሞ መሠረታዊ አሀዶችን በማዋሃድ በሚገኙ ሌሎች አሀዶች ለመጠቀም እንዲቻል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወስኗል። በዚህም መሠረት ለርዝመት ሜትርን፣ ለክብደት ወይም ለመጠነ–ቁስ ኪሎ ግራምን፣ ለሞሎኪውሎች መጠን ሞልን፣ ለጊዜ ሰኮንድን፣ ለልከ–ሙቀት (Temperature) ኬልቪንን፣ ለኤሌክትሪክ ኸረት (Electric current) አምፔርንና ለብርሃን ብክረት (intensity of light) ካንዴላን በአገልግሎት ላይ ለማዋል ተችሏል። በዚህም የሠለጠነው ዓለም በሜትሮሎጂ ዕርዳታ አንድ ወጥ ቋንቋ መነጋገር ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ለምሳሌ ከአሜሪካ ወደ አውሮፓ፣ እስያ፣ አፍሪካ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ወይም ወደ መሳሰሉት ሌሎች አገሮች "በኪሎ ግራም" ተለክቶ የተላከ ሸቀጥ በተላከለት አገርም በኪሎ ግራም ተመዝኖ ያለልዩነት ተቀባይነት ያገኛል። ስለሆነም ኪሎ ግራም በላኪና በተቀባይ መካከል የመግባቢያ ቋንቋ ሆኖ አገለገለ ማለት ነው። በዚህም ሜትሮሎጂ ጤናማ የሆነ የንግድ ልውውጥ፣ የኢንፎርሜሽንና የመረጃ ሥርጭት፣ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግር በአገሮች መካከል እንዲስፋፋ መሠረታዊ መዋቅር ሆኖ ያገለግላል።

ሜትሮሎጂ ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ የማይነጠልና ለኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ሕይወት መሻሻል በሚደረግ ሂደት ጉልህ አስተዋፅዖ የሚያበረክት የዕድገት መሠረት ነው። በዕለት ተዕለት ሕይወታችን በአለካክ እንድንጠቀም ግድ ከሚሉን ሁኔታዎች ጥቂቱን መጠቃቀስ ይቻላል።

የዕለት ጉርሳችንን፣ የዓመት ልብሳችንን ለመሸመት ገበያ ስንወጣ ወይም በማናቸውም አገልግሎት ለመጠቀም ስንሻ ለምንገዛው ምርትም ሆነ አገልግሎት ክፍያ መፈፀማችን የማይቀር ነው። ለከፈልነው ዋጋ ተመጣጣኝ ምርት ወይም አገልግሎት ስለማግኘታችን ወይም ገንዘባችንን በከንቱ ለመበተናችን ማረጋገጫችን ሜትሮሎጂ ነው።

ቡና፣ ስኳር፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ወይም ሥጋ ስንገዛ ነጋዴዎች በተሳሳቱና በአባይ መመዘኛዎች ለክተውልን ወይም ሠፍረውልን ቢሆንና ለከፈልነው ዋጋ የማይመጥን አነስተኛ ሸቀጥ ቢሸጡልን ተበዳይ መሆናችንን የሚያረጋግጥልን የአለካክ ሳይንስ ነው። በንግዱ መስክ ሸማቹ ከተሳሳቱ ሚዛኖችና መሥፈሪያዎች እንዲጠበቅ ሜትሮሎጂ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ማለት ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ እነዚሁኑ ሸቀጦች ስንገዛ የተሳሳተው ወይም አባይ የሆነው ሚዛን በትክክል ባለመለካቱ ምክንያት ከምንከፍለው ገንዘብ ያልተመጣጠነና የበለጠ ቁሳቁስ እንዲሸጥልን ቢያደርግ ነጋዴውን ኪሣራ ላይ ይጥለዋል። በነጋዴው በኩልም ሲታይ ይህን ከመሠለ ጉዳትና ኪሣራ የሚያድነው ጤናማ የሆነ የአለካክ ሥርዓት ወይም ሜትሮሎጂ ሥራ ላይ ሲውል ነው።

በሕክምና መስክ የተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች እንደ ደም ግፊትና የመሳሰሉትን በሽታዎች ለማወቅ መለካት አለባቸው። የመለኪያ መሣሪያዎቹ የተሳሳቱ ወይም በትክክል የማይሠሩ ከሆነ ጤነኛው ሰው በሽተኛ ነህ ተብሎ ለሕመምተኛ የተዘጋጀ መድኃኒቶች ለመውሰድ ይገደዳል። የዚህ ውጤት ደግሞ የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

በመድኃኒት ቅመማ ወቅትም የእንክብሎች ወይም የፈሳሽ መድኃኒቶች መጠን መለካት አለበት። መጠኑ ካነሰ መድኃኒቱ ሕሙማንን የመፈወስ አቅም አይኖርም። መጠኑም ከበዛ ፈዋሽነቱ ይቀርና የመርዝ ያህል ሆኖ እስከ ሞት ሊያደርስ ይችላል። በፋብሪካ ተመርተው የሚወጡ

ሸቀጦች በተወሰኑ ልኮች መሠረት ካልተዘጋጁ ለታቀዱላቸው ተግባራት ሊውሉ አይችሉም።

በሳይንሳዊ ምርምርና የቤተ–ሙከራ ክንዋኔዎች ሂደት ትክክለኛ ውጤቶች የሚገኙት በመለካት ነው። ከመርፌ አንስቶ ለታላላቅ ኢንዱስትሪዎች እስከሚውሉ መለዋወጫዎች ድረስ ጥራትና ደረጃቸው አስተማማኝ የሆኑ ምርቶች ለማግኘት የአለካክ ሳይንስ ጉልህ ድርሻ አለው።

ትክክለኛነታቸው ባልተረጋገጠ የመለኪያና የመሥፈሪያ መሣሪያዎች መጠቀም በንግዱ ዓለም የተዛባ ግብይትን፣ በሕክምና መስክ የጤንነት መቃወስንና የሕይወት መቀጠፍን፣ በሣይንሣዊ ምርምርና የቤተ–ሙከራ ክንዋኔዎች የተዛቡ ውጤቶችንና በሌሎችም ዘርፎች ተመሳሳይና የጎሉ ችግሮች የሚያስከትል በመሆኑ የመለኪያና የመሥፈሪያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊትም ሆነ አገልግሎት በመስጠት ላይ እያሉ በየጊዜው ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

የታላላቅ ኢንዱስትሪዎች መለዋወጫዎች፣ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ለዓለም ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የንግድ ሸቀጦች በአለካክ ሣይንስ ተደግፈውና ተረጋግጠው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሜትሮሎጂ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረክታል።

የትኛውም አገር ቢሆን ከሌሎች አገሮች ግንኙነትና ከዓለም ሕዝቦች ተነጥሎና ተገልሎ ደሴት ሆኖ ሊኖር እንደማይችል የታወቀ ነው። ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ፍሬዎች ከሀገሮች መልካም ግንኙነቶች የሚገኙ የጋራ ሀብቶች ናቸውና!

በንግድና ኢንዱስትሪ መስፋፋት ምክንያት የሚፈጠሩ ተፈላጊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አንዱ ከሌላው ለማግኘት መለዋወጥም ሆነ መገበያየት በአገሮች መካከል የነበረ፣ ያለና የሚኖር ነው። ይህ ሊሠምር የሚችለው ደግሞ አምራችና ሸማች አገሮች አንድ ዓይነት የአለካክ

ሥርዓት ሲከተሉና መግባባት ሲችሉ ነው። ምርቶችን በተመሳሳይ ሁኔታ መለካት ካልተቻለ የቴክኖሎጂ ሽግግርም ሆነ የንግድ ልውውጥ ስኬታማ ይሆናል ለማለት ያስቸግራል።

ስለዚህ ሜትሮሎጂ ከደረጃዎች ዝግጅትና አተገባበር ጋር ያለው የጠበቀ ግንኙነት ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው። የማንኛውም ምርት ወይም አገልግሎት ተፈላጊ ባሕርይ በትክክል ተለክቶ መታወቅ ስላለበት ደረጃ ይዘጋጅለታል፤ መመዘኛ ይወጣለታል ማለት ነው። ምርትም ሆነ አገልግሎት በተዘጋጀለት መሥፈርት መሠረትና በጥራት ስለመከናወኑ መረጋገጥ አለበት። በዚህ የማረጋገጥ ሂደት ሜትሮሎጂ ጉልህ ድርሻ አለው።

ከተለያዩ አገሮች የሚመጡ ምርቶችን በመገጣጠም ለአንድ አገልግሎት ማዋል እንዲቻል ሜትሮሎጂ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ በሚከተለው ምሳሌ ይብራራል።

በቻይና አገር የተሠራ የእጅ ባትሪ በሀገራችን ይሸጣል። ባትሪ ድንጋዩ የሚመረተው ግን በአገራችን ነው። የባትሪ ዓይን ደግሞ ከሆላንድ አገር የሚመጣ ነው። እነዚህ ሦስት ምርቶች በተለያዩ ሦስት አገሮች በወጡላቸው ደረጃዎች መሠረት በሚመረቱበት ጊዜ በመለኪያ መሣሪያዎች ምክንያት የቁመትና ወርድ ልዩነት ቢፈጠር ምርቶቹ እርስ በርሳቸው የሚገጣጠሙ ሳይሆኑ ይቀርና ለታቀዱለት ተግባር ሊውሉ አይችሉም። ነገር ግን የእጅ ባትሪው፣ ባትሪ ድንጋዩና የባትሪው ዓይን በወጣላቸው መሥፈርት መሠረት በትክክለኛ መሣሪያ ተለክተው ሲመረቱ ሦስቱም ተገጣጥመው ያለችግር የባትሪ አገልግሎት እንድናገኝ ያስችሉናል። ይህ ነው እንግዲህ ለአንድ ዓላማና አገልግሎት የተዘጋጁ የተለያዩ የምርት ውጤቶች በዘመናዊ ሁኔታ በትክክል ተለክተው የመሠራታቸው ውጤት የሚያስገኘው ጥቅም።

በአጭሩ ትርጉም ያለው የቴክኖሎጂ ዕድገትና የኢኮኖሚ ብልፅግና ላይ ለመድረስ የአለካክ ሣይንስ ወሳኝነት ያለው በመሆኑ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ የሚገኙ አገሮች

ኢኮኖሚያቸውን በማሳደግ ከሠለጠነው ዓለም ጋር ጎን ለጎን ለመራመድ እንዲችሉ ለሜትሮሎጂ ዘርፍ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።